Volume 1, July 1998 Issue No. 4

# Economic Focus

# ልሳነ ኢኮኖሚክስ

## Bulletin of the Ethiopian Economic Association (EEA)

*Dr. Eshetu Chole 1945 - 1998*



## In this Issue


- ለአዘጋጁ
- Dr. Eshetu Chole 1945 - 1998
- Food Security & Rural Land Policy: A Discussion
- Ethio - Eritrean War
- Economic Issues / Information
- Major Economic NEWS in the Last Two Months


(See details on the outer page of the back cover)


Editor: Alemayehu Geda

Editorial Board: Dr. AssefaAdmassie, Dr. Sentayehu Teferra, Ato Getachew Yoseph, Dr. Tesfaye Teklu, Ato Shiferaw Jammo

Volume 1, July 1998 Issue No.4

# Editorial

Two major tragedies have visited us since our last publication of *Economic Focus*. The first one was a tragedy very close to the heart of our Association and a great loss to our country, and, certainly, to our profession and our association. On June 18, 1998 we lost one of the founders of the Ethiopian Economic Association and its first president, Dr. Eshetu Chole. We remember Dr. Eshetu not only for his outstanding scholarship and his dedication and open mindedness in his teaching of economics, but also for his commitment to the economic developmentof our country and his unflinching stand on matters that he believes to be true. At a time when truth in general and true professionalism in particular were mercilessly crushed and replaced by blind adulation of the powers to be, he chose to go to prison rather than be an intellectual mercenary. When blind opportunism turned many an intellectual into a cannon fodder in the service of all kinds of dictators, Dr. Eshetu maintained his professional integrity and taught economics as he knew it. We hope his numerous students who are currently working as professionals in the field and those who were not fortunate enough to attend any of his classes, but knew him from his academic writings or as members of our Association, have learnt from his life not only a deeper understanding of economics but, more importantly, a commitment to the search for truth and duty to country and fellow humans. Here in the Association and the Editorial Board of our publications in which Dr. Eshetu was a member till he died, we are going to miss him dearly both as a valuable friend and a colleague. We would like to use this opportunity to extend our heartfelt condolences to his family in the name of all members of our Association. We also give our solemn promise to do our best to pursue the work he started with the professional integrity that he would expect from our Association were he still with us. To commemorate Dr. Eshetu's life and work we have dedicated this issue of *Economic Focu* for him and put together his vision of EEA and Abrar's contribution to our readers.

The second tragedy was even larger in that it affects the life of millions of our citizens and seriously challenges the sovereignty of our country. This tragedy relates to the war of aggression, engendered by the reckless leaders of Eritrea. A lot has been said, from different dimensions, about this mindless conflict since it started about a month and a half ago. As economists we strongly feel that the economies of both countries cannot afford another round of regional conflicts although we believe the effect will be worse on Eritrea than on Ethiopia. The effect of war on national economies, especially in countries that have no armament industry and have to use scarce foreign currency to acquire them, is not limited to the actual loss of life and destruction of property that directly ensue from it. The psychological effect that war has on domestic and foreign investors, on foreign tourists and the tourism industry in general, the general sense of instability it creates are very serious, with enduring effect on poor economies.

One of the issues that frequently arise about the rational behind Eritrea's decision to go to war (at least from their leader's perspective) is the differences in the economic polies of the two countries that culminated in the issuance of *Nacfa*. We asked one of our members, Getachew Belay, to visit this issue briefly as a way to provoke a discussion. Our regular contributor, Tekalign, claims that the cause of the conflict emanates from the political history of the region where all kinds of policy-issues, including the crucial issue of war and peace, are decided by a narrow group of elites without any consultation with the larger public. He contends that without opening the political spaces as to include civil society in the policy-making process, such conflicts are inevitable in this region. We have included this paper here to broaden the scope of the debate. We would like to hear more on this issue from our readers as it is crucial to the future of our country.

As we have said repeatedly, the purpose of this Bulletin is to generate broad discussion on matters of economic policy. Accordingly we were quite pleased to have received a number of articles in reaction to the debate on food security and rural land policy that appeared in Vol. I No.2 of *Economic Focu*. We have included a number of these articles in this issue.

This issue of *Economic Focu* also includes our regular features of Economic NEWS and issues. As always, we hope and invite our readers to join in these debates, for the purpose of this bulletin is to promote reasoned public debate on policy-issues that concern our country.

*Partiallysponosred by Friedrich Ebert Stifutung of Germany*

## SUBSCRIPTION

| Annual | Ethiopian | Africa | RoWorld |
|---|---|---|---|
| Non-members | Birr 22.80 | USD 10.00 | USD 15.00 |
| Members | | | |
| Institutions | Birr 11.40 | USD 5.00 | USD 7.50 |
| Individuals | Birr 16.00 | USD 7.00 | USD 10.00 |

Per copy

| | |
|---|---|
| Birr 3.50 excluding postage | USD 0.60 excluding postage |
| Birr 3.80 including postage | USD 1.00 including postage |

If you want to subscribe, please mark your preference and send this slip back to the Secretariat. (You will find the address on the front cover.)


# Notes to Contributors

The main objective of EEA Bulletin is to initiate policy-relevant public discussion on national and African economic issues. It presents synopses of research papers, panel discussions, public lectures, readers' comments and new research findings and notes.

Readers and contributors are encouraged to submit short articles (not more than 5 pages in double space with 12pt font size) preferably accompanied by an electronic version. If accepted, an edited version of the article will be sent to the author before publication. If the author does not respond within a week, the edited version will appear in the Bulletin.

Unaccepted articles will not be sent to the author(s).

We accept articles in both English and Amharic.

Views expressed in the Bulletin are those of the authors and are not necessarily of the institution's in which the author(s) work or of the EEA.

Articles should be addressed to:


The EEA Bulletin
Ethiopian Economic Association
P.O.Box 34282

Volume 1, April 1998 Issue No. 3

# ለአዘጋጁ

አቶ ሰኢድ ኑሩ

ባለፈው የ "ልሳነ -ኢኮኖሚክስ" እትም በ "Economic information" አምድ ሥር "የክልሎች የገቢ ድልድል ተመክሮ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ አንድ ጽሁፍ ማቅረቤ ይታወሳል::

የቀረበው ጽሁፍ እስካሁን የሚሠራበትን ሁኔታ የሚገልጽ ሲሆን ለውይይት መድረክ ከፋች ይሆናል በሚል እምነት፣ በተለይ በ "ድጎማ" ቀመሩ ዙሪያ ያሉኝን አንዳንድ አስተያየቶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ::

1990 የበጀት ዓመት በተሠራበት የ "ድጎማ" ቀመር ውስጥ አንደኛው መስፈርት በልማት የኋላ-ቀርነት ደረጃ ሲሆን፣ ይህም የተለያየ መስፈርቶችን አካትቶ ነበር:: ነገር ግን በከተሞች ከፍተኛ ችግር ሆኖ የሚገኘው ሥራ-አጥነት በመሆኑ የአዲስ አበባ፣ የሐረሪና የድሬዳዋ ከተሞችን የልማት ደረጃ ከፍ ስለሚያደርግና በእንጻሩም የተገለበጠውን አኃዝ ዝቅ ስለሚያደርገው በዚህ መሥፈርት የሚያገኙትን ድጎማ ዝቅ እንዲል ያደርገዋል:: በሌላም በኩል በአሁኑ ወቅት የሚደረገው የኢንቨስትመንት መጠን የወደፊቱን የክልሎች ዕድገት በእጅጉ ስለሚወስን በህዝብ ብዛት የተስተካከለ የኢንቨስትመንት ካፒታል መጠን ቢካተት ተገቢ ይሆናል::

"Regional Development and Overall Macroeconomic Performance in Ethiopia" በሚል ርዕስ በጻፍኩት ጥናታዊ ጽሁፍ በ 1990 የበጀት ዓመት በተሠራበት የ"ድጎማ" ቀመር ውስጥ ከተካተቱት የኋላ-ቀርነት መመዘኛዎች በተጨማሪ የክልሎችን የሥራ-አጥ ምጣኔ፣ በህዝብ ብዛት የተስተካከለ የኢንቨስመንት ካፒታል መጠን፣ አንድ ሰው በህይወት የሚቆይበት አማካይ ዕድሜ (longevity) እና ከማይምነት ነፃ የሆኑ ዜጎችን ብዛት ምጣኔ በመጠቀም የክልሎችን የልማት ደረጃ ለመገመት ሞክሬያለሁ:: የክልሎች የሀብት ውጤት ማጠቃለያ (regional income account) ያልተዘጋጀ በመሆኑ ምናልባት ዋነኛ የክልሉ የልማት ልዩነት አመልካች ሊሆን ይችል የነበረውን የክልሎች የነፍስ-ከፍ ገቢ መጠቀም አልቻልኩም::

| ክልል | በ1990 በሥራ ላይ የዋለ | | | ሌሎች መሥፈርቶች በመጨመር የተስተካከለ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጥምር አመልካች | ደረጃ | የተጠጋጋ ድርሻ | ጥምር አመልካች | ደረጃ | የተጠጋጋ ድርሻ |
| ትግራይ | 0.0411 | 8 | 4% | 0.078984 | 4 | 8% |
| አፋር | 0.0335 | 10 | 3% | 0.049502 | 10 | 5% |
| አማራ | 0.0498 | 5 | 5% | 0.076870 | 6 | 8% |
| ኦሮሚያ | 0.0492 | 6 | 5% | 0.0774448 | 5 | 8% |
| ሶማሌ | 0.0283 | 11 | 3% | 0.077403 | 11 | 3% |
| ቤኒሻንጉል/ጉምዝ | 0.432 | 7 | 4% | 0.028472 | 7 | 7% |
| ደ.ኢ.ብ.ብ.ህ | 0.0387 | 9 | 4% | 0.060225 | 9 | 6% |
| ጋምቤላ | 0.0520 | 4 | 5% | 0.069495 | 8 | 7% |
| ሀረሪ | 0.1961 | 2 | 20% | 0.013367 | 2 | 13% |
| አዲስ አበባ | 0.3044 | 1 | 30% | 0.0251271 | 1 | 25% |
| ድሬዳዋ | 0.1636 | 3 | 16% | 0.100111 | 3 | 10% |




ከዚህ በላይ በሠንጠረዡ እንደተመለከተው የሥራ-እጥነት በመሥፈርትነት መካተት የአዲስ አበባን፣ የሓረሪንና የድሬዳዋን የልማት ደረጃ አመልካችና ድርሻ ዝቅ ያደረገው ሲሆን የኢንቨስትመንት መካተትም የተጋነነ ደረጃ ተሰጥቷቸው የነበሩትን እንደጋምቤላ የመሳሰሉትን ክልሎች የልማት ደረጃ አመልካች ቀይሮታል።

ከዚህም በተጨማሪ፣ በተደጋጋሚ በድርቅ የመመታትን ሁኔታ (የተጠቂ ህዝብ ብዛትና የድርቅ ተደጋጋሚነት)፣ የማስፈፀም አቅም (physical performance)፣ ከማህል አገር በሚኖር ርቀት ምክንያት የሚፈጠር የገንዘብ የመግዛት አቅም፣ የክልል የቆዳ ስፋትና የልማት አመቺነትና የመሳሰሉት በቀመሩ ቢካተቱ የተሻለ እንደሚሆን ክልሎች አስተያየት ይሰጣሉ። በመጨረሻም ለውጭ ንግድ አመቺ የሆኑ እንደ ቡና፣ የቅባት እህልና የመሳሰሉትን በብዛትና በጥራት ለሚያመርቱ ክልሎች ልዩ ድጎማ ቢኖር በክልሎች ትኩረት ተሰጥቶት የምርቶች በስፋትና በጥራት መመረት ሊበረታታ ይችላል።

በመጨረሻም ከሠንጠረዡና ከስዕሉ ልንረዳው የምንችለው ነጥብ በተስተካከለው የልማት ደረጃ መመዘኛ መሠረት ለዲስ አበባ፣ ሀረሪና ድሬዳዋ በተከታታይ ከፍተኛውን ደረጃ የያዙ መሆኑንና በአማራ፣ በትግራይና በኦሮሚያ መካከል የጎላ የልማት ልዩነት አለመኖሩን ነው። ከነዚህ ክልሎች ቀጥሎ ተመሣሣይ የልማት ደረጃ ያላቸው የቤኒሻንጉል/ጉሙዝና የጋምቤላ ክልሎች ናቸው፡፡ የሶማሌና የአፋር ክልሎች በ3% እና በ5% በተከታታይ የመጨረሻውን ደረጃ ሲይዙ የደ.ኢ.ብ.ብ.ህ (ደቡብ ኢትዮጵያ) ክልል በ6% የቤኒሻንጉል/ጉሙዝና የጋምቤላ ክልሎችን ይከተላል።

<u>ከአዘጋጁ</u>

አቶ ሰኢድ ኑሩ ይህንን ወቅታዊና ጠቃሚ ነጥብ ስላመለከተን እያመሰገንን አንባቢዎች በዚህ ነጥብ ዙሪያ የምትልኩልንን አስተያየቶች በሚቀጥሉት የ ልሳን ኢኮኖሚክስ እትም ለማውጣት ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን።

# Dr. Eshetu Chole 1945 - 1998

## *Ethiopia has lost one of her best and brightest Economist*

It is with great sadness and shock that EEA members learned about the untimely death of the founder and the source of inspiration of their organization, Dr. Eshetu Chole. Had it not been for Dr. Eshetu and his colleagues the EEA would not have been what it is now. Dr. Eshetu was so committed to the causes of EEA that, even towards his last days, he went through one of the issues of our *Economic Focus* and provided us with his usual useful comments. He was also the co-organizer of EEA's project on Ethiopian economy.

EEA members, while mourning his untimely death, need to uphold the principles for which he was committed. Dr. Eshetu was committed to seeing Ethiopian economists being organized, tackling the endemic problem of poverty and being advanced in their profession. It is with this vision that he took the responsibility of organizing EEA. In his opening remarks during the inaugural ceremony of the EEA he expressed his feelings by saying: 'today it is a day we note with both embarrassment and pride: Embarrassment because it is only now that we have managed to establish our Association...but pride because the honor of forming the Association has fallen on us'. He continued, 'those of us assembled here today can legitimately tell our children that we were present at the creation. And on a personal level, I am not unconscious of my unique honor in serving as the first president of the EEA".

He was constantly warning his fellow economists to be professionals, open to criticism and be critical of power abuse. He emphasized: 'in past professional economists in Ethiopia remained largely untapped, partly because it was pointedly ignored; partly because it was listened to only to the extent it served the designs of the powers that were; and partly because on occasion they allowed themselves to be manipulated for ends that were at variance with the interests of the Ethiopian people'. Perhaps based on his agonizing experience from his prison days he noted: 'power bred arrogance, and arrogance was taken as a substitute for knowledge'. Such a negative attitude, according to Dr. Eshetu, 'was generic to those whose comparative advantage resided not in knowledge, but in marshaling the means of violence'. His use of the past tense in the above phrases seem to indicate that Dr. Eshetu was wishing not to have any one experiencing that. For those who happened to be on power his message was clear and simple: 'in more literate societies, there is a healthy interaction between power and ideas; in our, unfortunately, the relationship is one of studied distance at best, and outright hostility at worst. Since the country is the ultimate loser from this state of affairs, it is a situation that must be rectified'. Thus, Dr. Eshetu was also teaching his fellow economists and those in power to share his vision.

Dr. Eshetu was also advising Ethiopian economists to be open to self-criticism. He noted 'our profession makes no claims to infallibility; on the contrary, it is a field in which self criticism is often taken to great length. Our analysis may sometimes be wrong; our projections may often be off mark; and our prescriptions may not always work. But we are often our own severest critics. However, our self-indictment must not be used by outsiders as a convenient excuse for refusing to listen to us. For the price of disregarding economic opinion

is to open the gates wide to charlatanism of all sorts and to the pursuit of quick-fix solutions, which - unfortunately- do not exist in reality.'

What makes Dr. Eshetu unique as an economist is his exclusive interest in development studies in general and the importance of multi-disciplinary studies in Ethiopia in particular. In one of his addresses to EEA members he emphasized the challenge facing Ethiopian economists in the fight against poverty which, according to Dr. Eshetu, requires all disciplines to work together. Underscoring the importance of establishing EEA he noted: 'the significance of establishing EEA transcends the economics profession. It is my hope and conviction', he added 'that this inaugural ceremony [of EEA] will act as a spur to the formation of other professional associations particularly in our neighboring disciplines. Only with the mushrooming of such association will Ethiopia's arid intellectual environment be transformed into a green pasture of ideas. I yearn for the day when we will be able to organize joint activities with other associations and, acting in concert, raise the level of public discourse in our country to higher, more dignified and more constructive levels'. Though we mourn his untimely death, we are happy that he at least saw the mushrooming of different associations in our neighboring disciplines and the launching of our *Economic focus* and round table discussions before his last days.

Dr. Eshetu had a vision for EEA. He wrote 'my vision is that, say by the time it [EEA] celebrates its twentieth anniversary, it will have expanded its membership substantially; established a reputation as respectable repository of professional knowledge; accumulated a distinguished record of research and publications; further advanced the cause of public education in economics; earned the respect of the public; and contributed in several tangible ways to the economic advancement of Ethiopia'. Dr. Eshetu has clearly outlined what the focus of EEA should be. In his own words EEA should be 'entirely professional. The mechanisms for promoting the objectives of the EEA include publishing Journals and newsletters and -eventually - occasional papers and books (as well as teaching materials); organizing seminars, panel discussions, and lectures; and conducting and/or coordinating research on Ethiopian economy.' Recent events at EEA are broadly following Dr. Eshetu's vision. Finally let us repeat Dr. Eshetu's call for Ethiopian academics in general and Ethiopian economists in particular. On one occasion he said: "let us build a foundation of which we as founders will be proud, and for which our successors will be grateful. In the immortal words of John Donne, 'ask not for whom the bell tolls, it tolls for thee'". Weh hope we will live up to his expectation and will always remember what a great economist Ethiopia has lost.

HIS JOURNEY'S JUST BEGUN

Don't think of him as going away, his journey's just begun,  
Life holds so many facet - this earth is only one.  
Just think of him as resting from the sorrows and tears,  
In a place of warmth and comfort where there are no days and years.  
Think how he must be wishing that we could know today,  
How nothing but our sadness can really pass away.  
And think of him as a teacher survived by his thousands of students,  
And as living in the hearts of those he touched...  
For nothing loved is for ever lost, and he was loved so much.

Let God save his soul in Heaven and give His comfort to his family.

Shimelis G. Yae (one of his students - E-mail message )

# ጋሼ እሸቱ አልሞተም (ክፍል አንድ)

አቶ አብራር ሱሌማን
ኢኮኖሚክስ ዲፓርትሜንት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ሁለት ዓይነት ሻማ

ሰዎች ኢታልቅሱ፣ ለምንድነው ልቅሶ፣
ማለቱ ለማይቀር፣ ሻማ ተለኩሶ።
ሻማን የማታውቁ፣ ጥቅሙ ያልገባችሁ፣
ነዶ በወደመ፣ ከንቱ ታዝናላችሁ።
ብርሃኑን ሳይሰስት፣ ካበራ ለሁሉም፣
ቢጠፋም ግድ የለም፣ሻማ ነዶ ቢያልቅም።

እኔ ሻማ 'ምለው፣ ዓይነቱ ሁለት፣
አንዱ በጭለማ፣ ሌላው በንጋት።

ምንም ያለ ቢሆን፣ ደርሶ መቆጨቱ፣
የፈዘዘው ሞልቶ፣ እሸቱ መጥፋቱ።
ሻማው ሌላ ሻማ፣ ወልዶ ከለኮሰ፣
ጨረሩ ፈንጥቆ፣ ሀገር ካዳረሰ፣
ሥራው ህያው ሆኖ፣ ትውልድን ካደሰ፣
ቢያሸልብ ምን አለ?

እኔ ሻማ 'ምለው፣ ዓይነቱ ሁለት፣
አንዱ በጭለማ፣ ሌላው በንጋት።

ተለኩሶም እንኳን፣ ማድመቅን ያልቻለ፣
ብርሃኑን ሰስቶ፣ ሻማ እየመሰለ፣
በስሙ 'ሚነግድ፣ አረ ስንቱ እያለ፣
ድንገት ከሚጠፋ፣ ነዶ ያልታከተው፣
የጋን ውስጥ ሻማውን፣ ድርግም ባደረገው።

አንተ አያ ንፋስ፣ ዓይንህ የታወረው፣
ስስታሙን መርጠህ፣ እፍ! ብትል ምነው?

እኔ ሻማ 'ምለው፣ ዓይነቱ ሁለት ነው፣
አንደኛው በሌሊት፣ ብርሃን በሌለበት፣
ሌላው ግን በንጋት፣ ብርሃን በበዛበት።

(ለክቡር ዶክተር እሸቱ ጮሌ - ሰኔ 13 ቀን 1990 ዓመተ ምህረት)

በርግጥም አስደንጋጭ ዜና ነበር። ከስስትና ከፍፁም ራስ ወዳድነት በነፃ መንፈስ፣ ለሀገሩና ለወገኑ እጅግ ተቆርቋሪ የነበረ ሰዉ ማጣት መሪርና ጥልቅ ኀዘን ማስከተሉ የግድ ነው። ከራስ ጥቅም ይልቅ፣ ለሌሎች መኖርን አስቦና ወጥኖ፣ ይህን መሰሉንም ኃላፊነት በዘዴና በትህትና የሚያስተምር የራዕይ አባት ጋር አብሮ መሥራት መታደል የነበረውን ያህል፣ በማይቀረው ሞት እንደዋዛ በድንገት መቀማት ከማሳዘኑም በላይ፣ ያስቆጫል፣ ያናድዳልም። በሌላ በኩል ደግሞ፣ እንዲህ ዓይነቱ ክስተት ልብና ስሜትን በሲቃ ከማተራመስ አልፎ፣ ቆም ብሎ ማሰብንም ያስከትላል። ስኮን ብሎ ማውጠንጠን ይጠይቃል፣ በቅድሚያ ስለሟች፣ቀጥሎ ስለሌሎች፣ ከዚያም ስለራስ። ብቻ ስለሁሉም።

ከቀብር ስንመለስ፣ ከእኔ ይበልጥ ረዘም ላለ ጊዜ የሚያውቀውና የሥራ ባልደረባዉ የነበረ ወዳጄ ድንገት ዞር አለና፣ "አሁን አሁን ባሰበው በመሞቱ ኀዘን ሳይሆን ንዴት ነው የሚሰማኝ" ብሎ፣ ትንሽ ግራ ቢያጋባኝ፣ "እንዴት?" አልኩት። "ብዙ ነገር መሥራትና ትልቅ ቦታ መድረስ ሲችል ..." አለኝ። ወዲያው የኔን መልስ ሳይጠብቅ፣ "በሥለጠነው ዓለም ቢሆን?! ... ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ያለነው፣ አፍሪካ ነው ያለነው። ማለቴ፣ ብዙ የመሥራት ፍላጎትና ችሎታ በራሱ የትም አያደርስም" በማለት ለራሱ ሲያጉረመርም (ወይስ ጮክ ብሎ ሲያስብ)፣ ጆሮዬን ብቻ ነበር እንደዋዛ የሰጠሁት። ይህ ምልልሳችን፣ ብዙ ውስብስብ የኀሊና ጥያቄዎችን እንዳጫረብኝ ግን የኋላ ኋላ ነበር የገባኝ። ለምን አይቆጨው? ለምንስ አያንገበግበው? መቆጨት ሲያንሰው ነው፣ ወዳጄ። በጋሼ እሸቱ እንጎል ውስጥ የታጨቀውን የእውቀት ሀብት ጠንቅቆ ያውቃልና።

በዚህ ሁኔታ ነበር ወደ ቤቴ ያዘገምኩት። መሞቱን ስሰማም ሆነ ቀብሩ ላይ አላለቀስኩም ነበር። ሌሊቱን ብቻዬን ቁጭ ብዬ፣ ሞቅ ያለ ሥራ ላይ እንዳለሁ፣ ሳላስበው ዓይኖቼ እንባ አቀረሩ። ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ከፊቴ ተደቀነ፣ ወዲያውም ሳንዳፍታ ጭልም አለብኝ። እንባ ከቋጠሩት ዓይኖቼ ባሻገር፣ በዓይነ ኅሊናዬ አንድ ምስል ተመለከትኩ። ልክ ከአንድ ጠመዝማዛ ጎዳና እየተጓዝኩ ሳለ፣ ሻማ ይዞ ከፊት ለፊቴ ይመራኝ የነበረ አንድ የማውቀው ሰው በድንገት ተሰወረብኝ፣ ሻማውም በድንገተኛ ነፋስ ወደመ። በመጨረሻም የሚያስፈራ ጭለማ ሆነ። ሳላስበው ስለሻማና ብርሃን አሰብ ገባሁ። ሻማ ብርሃን ይሰጣል፣ ከተለኮሰ። የተለኮሰ ሻማ ሁሉ ደግሞ ደማቅ ብርሃን አይሰጥም። አንዳንድ ሻማ ሲለኩሱት እንደችቦ እየተንበገበገ ብሩህ ብርሃን ይሰጣል፣ በወጋገኑም ሌሎች እንደልብ ይንቀሳቀሳሉ፣ ህይወትም አለው። ሌላው ዓይነት ሻማ ደግሞ፣ ቢለኩስም ጥርት አድርጎ አያሳይም፣ ጭልጭል እያለ። እንዲህ ዓይነቱ ሻማ አንዳንዴ ከመኖሩ አለመኖሩ ይመረጣል፣ እንዳለ አስበውና በብርሃኑ ተማምነው መንገድ ሲጀምሩ አደናቅፎ ሊጥል ስለሚችል፣ አዘናግቶ ከቶውንም ገደል ይከትም ይሆናል። ለካስ ሻማ ሁሉ አንድ ዓይነት አይደለም?

የጋሼ እሸቱ ድንገተኛ ሞት የሀዘን ደራሽ ስሜት አድብቶ ውስጤን ያመሰው በዚህ መልክ ነበር። ስሜቴ ከኀዘን ወደ እልህና ቁጭት በመቀየሩ፣ ዕንባዬም በመፍሰስ ፈንታ ተመልሶ ወደ ጎራው ተከተተ። በዱልዱም ብዕሬ ጫፍ እንደ ዶፍ ዝናብ ባጎርፈውስ? የውስጤን። ጎርፉም ወዳሻው ይጉረፍ። ብቻ እግረ መንገዱን የቆሸሸ ኀሊናዬን በጠራረገልኝ?! ቀስ በቀስ፣ እእምሮዬ እየተረጋጋና እየሰከነ ሲኼድ፣ ከወዲያ ወዲህ ዥዋዥዌ የሚጫወተው የህሳብ ማዕበልም መልሀቁን መጣል ጀመረ። በመጀመሪያ፣ ሁሌ እንኳን ባይሆንም አንድ የሚወዱት፣ የሚያከብሩት ወይም የሚያደንቁት ሰው ሲሞት፣ ስለማንነቱና በህይወት በነበረበት ጊዜ

ስለሥራቸው ሥራዎች በጥልቀት መመርመር የተለመደ መሆኑ ታወሰኝ:: ማንነቱና ገቢሩ ገዝፈው የሚታዩትም አንድም ሲርቁት፣ አሊያም በሞት ሲለዩት ስለመሆኑ ከሊል ጅብራን "The Prophet" በሚለው መጽሀፉ ያሰፈረው ትዝ አለኝ፡ "When you part from your friend, you grief not; for that which you love most in him may be clearer in his absence, as the mountain to the climber is clearer from the plains." ከዚያም፡ ሰው በሞተ ቁጥር "እገሌ እንዲህ ነበር ... ያን ይወድ፡ ይህን ይጠላ ነበር ..." እያልን፡ በተለይ ደግሞ ጥሩ ጥሩ ነገሩን እያነሳን፡ ከንፈር እየመጠጥን፡ ሰው ከበላ ከጠጣ የግድ የሚፈልቀውን እንባ የመርጨት ባህላችን ከፊቴ ድቅን አለ:: ይህን ባሰብኩ ጊዜ፡ የጥፋተኝነት ስሜት ጎሊናዬን ይሞግተው ጀመር:: እንደዚያ ታሞ ሲማቅቅና ከዓመት በላይ ሲሰቃይ ሰምቼ ጆሮ ዳባ ልበስ ለምን አልኩ? እንዲህ እንዲህ እያልኩ፡ በሀሳብ ጎዳና የኋሊት ሸመጠጥኩ፡ ከጋሼ እሸቴ ጋር፣ ከራሴ ጋር፣ ከኢኮኖሚክስ ጋር፣ እንዲሁም ከሀገሬ ጋር:: የአንዳንድ ሰዎች ሞት በጎሊና ላይ ሳይወዱ በግድ የሚቆሰቁሰው እስጥ አገባ ከባድ ነው:: ምን ዓይነት ሰዎች ይሆኑ እነዚህ? ከተራ ሰው የተለዩና በቀላሉ የማይዘነጉ:: ታዲያ ጋሼ እሸቴን ከተራ ሚች የሚለየው ምንድነው? ይህ ሰው ከተራ ምሁር የሚለየው አንድ ነገር እንዳለ አጥብቆ ይሰማኝ ጀመር:: ጀግና ይሆን እንዴ? ጋሼ እሸቴ::

ጀግንነት ምንድነው? በርግጥ፡ ጀግንነት አንፃራዊ መሆኑ ይገባኛል:: በጊዜ፡ በቦታና በህብረተሰቡ ባህላዊ፡ ማህበራዊ፡ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ እምነቶች ይወሰናል:: ዞሮ ዞሮ ግን፡ ጀግንነት አገርን ከመውደድ ይመነጫል:: አገርን መውደድ ደግሞ በብዙ መልክ ሊገለፅ ይችላል:: የተለያዩ ደረጃዎችም አሉት:: በጎ ነገር ለሀገርና ለህዝብ መመኘት እንዱና የመጀመሪያው ሲሆን፡ የተመኙት እንዲሆን ሳያሰልሱና ሳያመነቱ ብርቱ ጥረት ማድረግ ሌላው ነው:: የተመኙት እንዲሆን እራስን 'መሰዋት' ደግሞ ከሁሉ የላቀ ነው:: ችግሩ (በተለይ በአገራችን)፡ ስለመስዋዕትነት በሰፊው የሚታወቀው፡ በዐውደ ውጊያ ውሎ ጉድል ሠርቶ ከመሰዋት ጋር የተያያዘው ነው:: በኔ እምነት፡ ይህ ጠባብና የተዛባ ትርጉም ነው፡ ለጀግንነት:: ለኔ፡ ጀግና የሚለው ቃል ከዚህ ትንሽ ሰፋ ያለ ሆኖ፡ ህይወቱን ከምንም ነገር በላይ ለሀገርና ለህዝብ ጉልህ ፋይዳ ላለው በጎ ነገር ያዋለ ሁሉ ጀግና ነው:: ይህ ሁሉ ጳር ጳር ማለቴ፣ ባጭሩ የምሁር ጀግናም መኖሩን ለመጠቆም ያህል ነው፡ መማሪያ ሳይጨብጡ፡ በአስተሳሰባቸውና በአመለካከታቸው ትልቅነት ሀገራቸውን የሚጠቅሙ:: ለመሆኑ፡ "መስዋዕትነት ማለት ተቃጥሎ ማለቅ ማለት ሳይሆን፡ እንደጧፍ ነዶ ለአገር ለወገን ብርሃን መሆን ማለት ነው::" ያለው ማን ነበር?

ምሁር ማለትሳ? በትምህርት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ወይም የላቀ ውጤት ያስመዘገበ? በተማረው ትምህርትና በሠለጠነበት ሙያ ሰፊ ጥናትና ምርምር ያደረገ? በርግጥ፡ ምሁርነትም እንደ ማኅበረ-ሰቡ አመለካከትና የዕድገት ደረጃ ሊለያይ ይችላል:: ከላይ የተጠቀሱት ለሀገር ጠቃሚ ቢሆኑም፡ ከነዚህ በተጨማሪ፡ እንድ ዜጋ ከተራ የሙያ ምሁርነት ባሻገር 'ጀግና ምሁር' ለመሆን፤ ከሠለጠነበት ሙያ ወጣ ብሎ ስለሌሎች ዲሲፕሊኖች ሁለገብ (multidisciplinary) ዕውቀቱን ማጎልበት፣ ለሀገሩና ለወገኑ ጠቃሚ በሆኑ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች (extra-curricular activities) በእጅጉ መሳተፍ፡ የህዝቡንም ችግር አብሮ መጋራት፡ ከሌሎች ጋር ተቻችሎ መሥራትና ማስተባበር ይጠበቅበታል:: በዚህ መልኩ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ የቻለ ምሁር፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ ሰብአዊ እሴቶች ሊኖሩት ይገባል፡ ቢያንስ የተወሰኑ:: ሰው ነውና ከሁሉ በፊት ጥሩ ሰው መሆን አለበት:: ብቻ እንደኔ እንደኔ፡ ፊደል የቆጠረ ወይም የተማረ (ካስፈለገም የተመራመረ) ሁሉ ምሁር ሊባል አይገባም:: ይህን ሁሉ የዘባረቅኩት፣ ባጭሩ ጋሼ እሸቴ ጀግና ነበር ለማለት ነው:: ዙሪያ መለስ ምሁር ነበርና:: ምናልባት ይህ ሰው ለአንዳንድ ሰዎች ኢምንት ሊሆን ይችላል:: ይህ እንግዲህ የአመለካከት ልዩነት ነውና ምን ይደረጋል?! ጋሼ እሸቴን ጀግና ምሁር ለማለት ያስደፈረኝ፡ በብዙ መልኩ በቀላሉ ምትክ የማይገኝለት መሆኑን ከመገንዘብ የመነጨ ከመሆኑም በላይ የሞራል ጥንካሬውና ወደር የለሽ ምሁራዊ ድፍረቱ እንደኔ ላሉ ታዳጊዎች በመልካም አርአያነት የሚጫወቱትን ሚና ግምት ውስጥ በማስገባትም ጭምር ነው:: በአንድ መልኩ፡ የእሱ ሞት የኃላፊነትንና ለሌሎች የመኖርን ድፍረት የገበየሁበት አጋጣሚም ሆኖ ይሰማኛል:: ስሙ በታሪክ ማህደር ተገቢውን ሥፍራ ሊቸረው የሚገባ መሆኑን አበክሬ የምገልጸውም፡ እራሱ በሥራው ውጤት ኒሻን ባይሸለምም፡ ኒሻን ሊሸለሙና ሊያስሸልሙ የበቁ በርካታ ሌሎች ዜጎችን ካፈሩ ጥቂት የሀገራችን የዘመኑ በሳል ምሁራን እንዱ እንደሆነ በማሌ ስለማምን ነው:: እናሳ?

እናማ በሌላ ቀን፡ ብጥቅጣቂ ወረቀቶቼን ብድግ አድርጌ እንደተለድ ማንበብ ተያያዝኩ:: እግረ መንገዴን፡ አንዳንድ ነገሮች ውስጤ ውል ውል ሲሉ ይሰማኝ ነበር:: እንብቤ ስጨርስ፡ ሳላስበው ብዙ መዘባረቁ ታወቀኝ:: ሆኖም፡ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም፡ ከሞላ ጎደል፡ የውስጥ ስሜቴን የገለፅኩ መሰለኝ:: ውስጤ ታምቆ የቀረ እንዳለም ገባኝ:: ታዲያ ለምን አልገላገልም? የጻፍኩትን ደግሜ ወጣሁት:: አሁን ማንበብነብ ሳይሆን፡ በደንብ አነበብኩት:: እንደ ጽሁፍ አላረካህ አለኝ:: አልማረከኝምም:: ርዕሱ፡ ጭብጡ፡ የቃላት፡ የሀረጎችና የዐረፍተ ነገሮች አሰካክ፡ የሀሳቦች ቅደም ተከተል፡ድምፀቱ ... ወዘተ? አይ አለማወቅ! የቲንቲ ችሎታ ማነስ! ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደር! ለመሆኑ፡ ምንድነው የምጽፈው? ለምን?

ስለ ጋሼ እሸቴ:: የማውቀውን፡ የሚሰማኝን:: ዓይኔ አይቶ፡ እዝነ ልቦናዬ እስተውሎ፡ ልቤ በክብር የመዘገበውን:: ስለልጅ እሸቴ ወይም ስለጎልማሳው እሸቴ ሳይሆን፡ ስለጋሼ እሸቴ:: ስለ አባት እሸቴ:: አእምሮው ብሩህ፡ አስተዋይና አመዛዛኝ፡ ልቡ ደግሞ ርህሩህና ደግ ስለሆነው ታላቁ የመንፈስ አባቴ:: ስለማን እንደምጽፍ በውል ሳጤን፡ "አበለሻሸው ይሆን?" ብዬ ሰጋሁ:: ማንኛና ስለሱ የረባ ነገር የምጽፈው? የት አባቴ አውቀውና? የቅርብ ጓደኛዬ አይደል! ወይ ደግሞ እንደዚያ ስሙ በገነነበት ዘመን ኖሬ የሠራውን ተአምር እንደሌሎቹ በአካል አላየሁ! በርግጥ፡ ተማሪው በመሆን፡ ለተወሰኑ ዓመታትም ቢሆን አብሬው በመሥራት ስለሱ የማውቃቸው አንዳንድ ነገሮች አይጠፉም:: ከዚህም ሌላ፣ ጽሁፎቹ ስለሚጥሙኝ ከተወሸቁበት አሳድጄ ጥቂትም ቢሆኑ አንብቤያለሁ:: ደግሞስ፡ ያየሁትንና የገባኝን ያህል ብጽፍ ምን አለበት? ሌሎች ደግሞ በበሳል አእምሮ፡ በሹል ብዕራቸው እኔ ያላስተዋልኩትን፡ የዘነጋሁትን (ወይም የተሳሳትኩትን

አርመው) ቢጽፉስ? ስለዚህ፣ ጋሼ እሸቱ በኔ ደካማ መነፅር ምን ይመስላል? የተዋጣለት መምህር፣ መልካም የሥራ አጋር፣ እንዲሁም ድንቅ የጥበብና የሥልጣኔ አባት:: እኔ ለጋሼ እሸቱ ጥሩ ልጅ ላልሆን እችላለሁ:: እሱ መፍጠር ይፈልግ የነበረውን ዓይነት:: በሆንኩ ደስ ባለኝ ነበር:: ግን አይደለሁም:: ጨርስ!-ታዲያ ጥሩ አባቴ እንደ ነበር ብመሰክርለትሳ? መቸም፣ ልጅ ስለአባቱ አይናገር አይባል!፣ ዕይታው ውሱን፣ ድርጊቱ ችኩል፣ ሀሳቡ ብስለትና አርቆ ማስተዋል የጎደለው መሆኑ ግልጽ ነው:: አይ የልጅ ነገር! በአካል እያደገ፣ በአእምሮው እየበሰለ ሲኼድ፣ የዕይታው አድማስ መስፋቱስ የት ይቀራል? ጋሼ እሸቱ የእውቀት ልጆቹን በጣም የሚያቀርብ፣ በእኩል ዓይን የሚያይ፣ ሀሳባችንን ሳንፈራ በድፍረት እንድንገልጥ የሚገፋፋን:: ስንሳሳት የሚቆጣን መሰላችሁ? እንዲያውም! ረጋ ባለ መንፈስ፣ እራሱን ዝቅ አድርጎ፣ በሚገባን ቋንቋ ስህተታችንን እንድናርም ነበር የሚያደርገው::

ይህን ያህል ከተንደረደርኩ ዘንድ፣ የዚህችን መጣጥፍ አርባና በግልጽ ላስቀምጥ:: ይህቺን ብጣቂ ማስታወሻ የጻፍኩበት ምክንያት፣ የዚህ ታላቅ ሰው ሥራ በእኔ እውቀትና ችሎታ ተመዝኖ የሚመሰከርለት ነው ከሚል ጭፍን የዋህነት የመነጨ ሳይሆን፣ ከዚህ ይልቅ ለሱ ያለኝን አድናቆትና ክብር ለማሳየት፣ በድንገተኛ ሞት መለየቱ ያሳደረብኝን ጥልቅ የኀዘን ስሜት ለመግለፅ አስቤ፣ በይበልጥ ግን ከሞቱ ጀርባ በኔ ህይወት ውስጥ ጥሎት ያለፈውን ሰናይ ምግባሩን ህሊናዬ ደፍሮ በዝም አይንቅዝም ችላ ማለትን ስላልተቀበለው ነው:: ምክንያቱም፣ የጋሼ እሸቱ ህልፈት ከልቤ ጋዳ የኀዘን እንጉርጉሮ ከመቀጠር አልፎ፣ ህሊናዬንም ሳይናገር ትቶልኝ በኼደው፣ የቤት ሥራ ጠቅጥቆታልና:: ዋነኛ ዓላማዬም፣ ጋሼ እሸቱ ስለሠራቸው ሙያዊ ሥራዎች ትንታኔ ለመስጠት ሳይሆን (አቅሙም የለኝም)፣ በጽሁፍ ትቶ ስላልኼዳቸው ድንቅ ተሰጥኦዎቹ እንደ ደቀመዝሙሩ፣ እንደ ሙያ አጋሩ (ወይም የሥራ ባልደረባው)፣ እንደ ሰው በተለይ እንደጥሩ አባት፣ ከሁሉም በላይ ግን እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በመሆን በግሌ ከተገነዘብኳቸው ውስጥ ጥቂቶቹን ለትውስት ያህል ለመወርወር ያህል ነው:: የሚያዝናና የሥነ ጽሁፍ ችሎታ ባይኖረኝም፣ አወላጋጂም ቢሆን፣ የዚህን ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ሥራ የሠራ ስሙጥር የኢትዮጵያ ባለውለታ ገድል፣ አቅሜ በፈቀደው ሁሉ ለማሳወቅ ካለኝ ከፍተኛ ጉጉት በመነሳት፣ ብሎም በሌሎች ልቡና ይህንኑ ለማሳደርና ለዚህ መሰሉ በጎ ተግባር ለማነሳሳት ብዬ ነው:: በተለይም በቅርብ በሚያውቁት ዘንድ:: ምናልባትም፣ እንዲህ ዓይነቱ ጅምር በብዙዎች ዘንድ ከቀን ወደ ቀን እየተብላላና እያደገ ኼዶ፣ ማን ያውቃል አንድ ቀን ወደ አንስተኛ ባዮግራፊ ሊያመራ ይችልም ይሆናል:: የዚህን አንጡራ የሀገር ልጅ ድንቅ ሰብእና እንደዋዛ ችላ ብዬ፣ ወደፊት ታሪክ ቢዘነጋው፣ እሱ ከሞት ተነስቶ ፍርድ ቤት አቁሞ ባይፋረደኝ እንኳን፣ ቢያንስ ህሊናዬ በውለታ ቢስነት ወንጀል ሲቆጠቁጠኝ መኖሩ መች ይቀርልኛል?

የጋሼ እሸቱን ስም በዝና የማውቀው ገና ድሮ የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ ነበር:: ከመምህሮቼ አንዱ ጋሼ እሸቱን ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ መልኩ ነበር ያስተዋወቀኝ:- " ዶክተር ጌታቸው ቦሎዲያ ምን እንዳለ ታውቃላችሁ?፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ተኩል ሰው ብቻ ነው ያለው:: አንዱ እኔ ነኝ፣ ግማሹም ዶክተር እሸቱ ጮሌ ነው::" ከዚያማ በዩኒቨርሲቲው የሶስተኛ ዓመት የኢኮኖሚክስ ተማሪ ሆኜ፣ ዲቬሎፕመንት ኢኮኖሚክስ የተባለውን ኮርስ ሊያስተምረን ብቅ ባለ ጊዜ፣ የልጅ አእምሮዬ በኩራት ተወጠረች:: ከመጠቀ ምናቡ፣ እጅግ ከነቃ አእምሮው፣ በረቀቀ ቋንቋውና በርቱዕ አንደበቱ ታግዞ፣ እነዚያን የዴቬሎፕመንት ሞዴሎች ተራ በተራ ሲያኾጎደጉዳቸው፣ አብዛኛውን ጊዜ በጣም ከመመሰጤ የተነሳ ሌክቸር መያዝ ይሳነኝ እንደነበር አስታውሳለሁ:: ይኸው ድንቅ የማስተማር ጥበቡ ይመስለኛል ብዙ የኢኮኖሚክስ ተማሪዎች ምን ጊዜም ኮርሱንና ጠቢቡን መምህር እንዳይዘነጉት ያደረገው::

በትኩረት ሳስተዋለው፣ ጋሼ እሸቱ ስለሚያስተምረው ኮርስ ብቻ ሳይሆን፣ ከአለባበስ ጀምሮ አንድ ሰው እንዴት ጥሩ መምህር መሆን እንዳለበትም ያስተምራል:: እንደዚሁም፣ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር እንደ አንዳንዶቻችን በክፍል ውስጥ መድረኩ የእኔ ነው በሚል ተልካሻ ሰበብና በማን አለብኝነት ከትምህርቱ ጋር ዝምድና የሌላቸውን አርዕስቶች እያነሣ ሲዘባርቅ በጭራሽ አይገኝም:: ከዚህም ሌላ፣ በሥራው እጅግ ጠንቃቃ፣ ዝርክርክነትንና ስንፍናን አጥብቆ የሚጠላ ለመሆኑ ብዙ ነቃሽ ማስረጃዎችን መስጠት ይቻላል:: ለምሣሌ፣ ከመቶ በላይ ለሆኑ ተማሪዎች ቴስቶችንና አጫጭር የምርምር ወረቀቶችን በየጊዜው እየሰጠ፣ እያንዳንዱን አርሞ፣ በጣም ማመን በሚያዳግት ፍጥነት ይመልስ እንደነበር ማንም የሚዘነጋው አይሆንም:: (ታዲያ ቀይ በቀይ የሚያደርገው ነገር!) ልክ አሁን ስለነዚህ ነገሮች እየከተብኩ ሳለ፣ ላንዳፍታ የስንፍናዬና የዝርክርክነቴ ነገር ፊቴ ድቅን በማለቱ፣ ከባድ ሀፍረት ነው የተሰማኝ:: "እርማት በዛ!... ሥራ በዛ!... ጊዜ የለኝም!... ወዘተ ..."፣ እያልኩ በሌለ የሥራ ውጥረት ያናፋሁት ሁሉ ትዝ አለኝና በባዶነቱ እራሴን ታዘብኩት:: ትቶልኝ የኼደውን ቢሮውንማ እንዴት መላ ቅጡን እንዳሳጣሁት ቢሰማ ምን ይለኝ ይሆን? እሱ እንኳን በመጠኑም ቢሆን ፈለጉን የሚከተሉ ሌሎች ሸጋዬ ልጆች ሞልተውት የለ? ይብላኝ እንጂ ለኔ:: ጠቅለል ባለ መልኩ፣ ጋሼ እሸቱ በማሳወቅ ጉጉት የተጠመደ፣ ለማወቅ የሚስገበገበውን ያህል ለማሳወቅም ብርቱ ጥረት ያደረገ፣ ተግቶ መማርንና በርትቶ መሥራትን ለደቀ መዝሙሮቹ በተግባር ያረጋገጠ! እንከን የማይወጣለት መምህር እንደነበረ ነው የማስታውሰው:: ምናልባት ከህይወቱ ግማሽ ያህል ዕድሜውን ለሰዋለት የመምህርነት ሙያ ከነበረው ልዩ ፍቅር ይሆን? በተለያዩ አጋጣሚዎች ይህንኑ ማረጋገጡን እናያለን:- "በመምህርነት በቆየሁባቸው ጊዜያት ሁሉ ተማሪነቴን ያቋረጥኩ አይመስለኝም::" "It has been a great joy to be a teacher." እያለ:: ምናልባትም ደግሞ የተዋጣለት መምህር የመሆኑ ምሥጢር ለኢኮኖሚክስ ከነበረው ፍቅርና አክብሮት የመነጨ ሊሆን ይችላል:: እራሱ ይል እንደነበረው:- "It was a great joy to be a student of economics."

መቸም እንደ ጋሼ እሸቱ የሚናገረውን ቋንቋ እጅግ

አቀላጥፎ የሚጠቀም ቢኖር በጣም ጥቂት ነው። ይህ ደግሞ ከአእምሮው ብሩህነት፣ ከአስተሳሰቡ ምጥቀትና ወደር የለሽ ትንጅት ጋር ተዳምሮ፣ ጥሩ የንግግር አዋቂ እንዳሰኘው አንኳር መረጃው በተናገረባቸው መድረኮች ሁሉ በቀላሉ አድማጭን የማነሁለልና የማሳመን ተሰጥኦው ይመስለኛል። እንዲሁ ሲታይ ጭምት፣ ግን የመድረኮች ሁሉ ንጉሥ መሆኑ፣ ገና በለጋ ዕድሜው ነበር በብዙዎች ዘንድ የተስተዋለው። ትዝ ይለኛል፣ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ምሥረታ በዓል ላይ፣ ክቡር ሚኒስትር ዶክተር አብዱልመጂድ ሁሴን የመዝጊያ ንግግር እንዲያሰሙ በተጋበዙበት ዕለት፣ ንግግራቸውን ያሳረጉት፣ ከጋሼ እሸቱ ጋር አብረው ተማሪ በነበሩበት ጊዜ ስለሠራው አንድ አስደናቂ ታሪክ የሚከተሉትን ሀረጎች በመቂጠር ነበር፤

" My mind keeps running to my student years in the now Addis Ababa University. Permit me to recall a happening that took place in 1965/66 G.C. That year, three highly distinguished students were running to become the president of the Addis Ababa University Students' Association. One of them was your present association's president, Dr. Eshetu Chole . The three candidates running for the office of the presidency waged extensive campaigns for weeks which finally culminated in three of them addressing the entire student body one after the other explaining their position on the issue of the day faced by the student body at large, and why one candidate was better than the other. When Dr. Eshetu's turn came to address the gathering, in his superb oratorical ability he delivered a stinging message that evening and concluded by remarking on the crucial issue of why he was better than his two rivals by simply saying, 'AS FOR ESHETU CHOLE, LET HISTORY SPEAK.' He won the presidency of the day."

ከዚህ በተያያዘ፣ እኔ ደግሞ በግሌ የማልረሳቸዉ አንድ ሁለት ገጠመኞቼን ባክልስ? የዛሬ ስድስት ዓመት ግድም በተደረገ አጠቃላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማህበር ስብሰባ፣ በአንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት፣ ከግራም ከቀኝም ከየፋኩልቲዉ እሉ የተባሉ ምሁራን ሀሳባቸዉን ተራ በተራ ሰነዘሩ። ነገሩ ከተጠበቀው በላይ በመንዛዛቱና ባጭሩ እልባት ባለማግኘቱ ትዕግሥታቸው ተሟጦ ይመስለኛል፣ የወቅቱ የማህበሩ ፕሬዚዳንትና የዕለቱን ስብሰባ ይመሩ የነበሩት ፕሮፌሰር፤ ከፊት ለፊታቸው ያደፈጠውን አንድ ጭምት ቢጤ "እባክህ ገላግለን" በሚል ዓይነት ሀሳቡን እንዲሰነዝር ይጠይቁታል። ይህ ሰው መናገር ጀመረ፣ በመጀመሪያ ዋናውን ጉዳይ ቁልጭ አድርጎ አስቀመጠ፣ ቀጥሎም አከራካሪ ነጥቦቹን ተንትኖ መልክ አስያዛቸው፣ በመጨረሻም መፍትሔ ብሎ ያሰበውን እንደቀልድ ወረወረ። አጀንዳው ተዘጋ። ፕሮፌሰሩም፣ የኔ ቢጤ የተምታታበትም፣ ብቻ ሁሉም "እፎይ!" አለ። በዚያኑ ሰሞን የዚሁ

ዩኒቨርሲቲ 'ታሪካዊው የልደት አዳራሽ' (በዚያን ዕለት የጋሼ እሸቱ አገላለጽ)፣ በወቅቱ የተማሪዎች ካውንስል አማካይነት ስለአዲሱ ህገ-መንግሥት ሙያዊ አስተያየቱን እንዲሰጥ ከሌሎች ሶስት ምሁራን ጋር ይጋበዛል። በተለመደው እንደበቱ፣ ገና አንድ ሁለት ዐረፍተ ነገር ተናግሮ ሳይጨርስ፣ ባልጠበቅኩት ሁኔታ አዳራሹን ጢም አድርጎ የሞላው ተማሪ ለረጅም ጊዜ ያጨበጨበውን እስካሁን አልረሳውም። ትንሽ ግራ ተጋባሁ እንጂ በዚህ አልተገረምኩም። በዚያኑ ዕለት ምሽት የቴሌቪዥን ዜና ላይ፣ የዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች ለጦርነት እንዳነሣሣ ተደርጎ መቅረቡን ባደመጥኩ ጊዜ ነበር በይበልጥ የተገረምኩት። ጋሼ እሸቱ በተናገረ ቁጥር ለራሱ ሳይታወቀው በአድማጩ ዘንድ የሚፈጥረውን ስሜት በየዋህነት ካለመገንዘብ፣ ወይስ ጠንቅቆ ከማወቅ በመነጨ ፍርሃት? እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የተናገረው ፍሬ ነገር ያን ያህል ማስጨብጨቡ በወቅቱ ለኔም ዱብ ዕዳ ቢሆንብኝም፣ አንድ ነገር ግን የስሜን ያህል አስታውሳለሁ፣ ከጦርነት ጋር አንዳችም ግንኙነት እንዳልነበረው።

ጋሼ እሸቱ ህይወት ካስከተለበት ህመም ጋር ተሟግቶ ሳይረታ ነበር ቅብጥብጥ ነፍሱ በዘለዓለማዊ ዕረፍትና ሰላም ጉጉት ወደ ሞት አጣድፋ የሰደደችው። በአጭር ተቀጨ ባይባልም እንኳን፣ ከኛ ከወጣቶቹ በላይ ትኩስ፣ ጎበዝና ጠንካራ አካላዊ ብቃት እንደነበረው የተገነዘብኩባቸው አጋጣሚዎችም ነበሩ። ትዝ ይለኛል፣ የዛሬ አምስት ዓመት ገደማ፣ ናዝሬት በአንድ ወርክ ሾፕ ላይ በነበርንበት ወቅት፣ አንድ ቀን ምሽት፣ 'አዳማ ራስ' ከሚገኘው የመዋኛ ገንዳ ፊት ለፊት ተሰባስበን፣ በሱ ጣፋጭ ቀልዶች እየታጀብን፣ 'ሻይ' ቢጤ እየጠጣን ስንዝናና፣ ሳናስበው ብዙ አመሸን። ታዲያ በማግስቱ አንዳንዶቻችን ከምሽቱ ድካም የተነሣ ከንቅልፋችን መነሣት እንኳን ሲያቅተን፣ የተቀረነው ደግሞ እንደምንም ከስብሰባው አዳራሽ የግድ ተጎልተን በደመ-ነፍስ ለመሣተፍ ስንሞክር፣ ጋሼ እሸቱ ግን ከሌሊቱ አስራ ሁለት ሰዓት ብድግ ብሎ ልክ እንደ ሃያ ዓመት አፍላ ጎረምሳ እየተንጎማለለ ስፖርት ቢጤ ሲሠራ እንደነበር አስታውሳለሁ።

የጋሼ እሸቱ ችሎታ (ክህሎት) ሰፊ ነበር። እውቀቱና ተሰጥኦው በኢኮኖሚክስ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። በተፈጥሮ የመጻፍ ፀጋ ለመቀባቱና የተባ ብዕረኛ ለመሆኑ ሥራዎቹ ይመሰክራሉ። በእንግሊዝኛም ሆነ በአማርኛ ቋንቋዎች ተራቆ መጻፍ ከመቻሉም በላይ፣ ጽሁፎቹም በረቀቀ ግን ግልጥ በሆነና እጅግ በተዋበ አገላለጽ የተነሡበትን ቁም ነገር ከማስተማር በተጨማሪ፣ የሚያዝናኑና ተደጋግመው ቢነበቡ የማይሰለቹ መሆናቸው ድንቅ የሥነ ጽሁፍ ተሰጥኦውን ያረጋግጣሉ። ለሥነ ጽሁፍ የነበረው ዝንባሌና ክህሎት ስለኢኮኖሚክስ ከጻፋቸው ጥናቶች አንስቶ፣ በተለያዩ መድረኮች ካደረጋቸው ንግግሮች መገንዘብ ይቻላል። በተለይም ተማሪ በነበረባቸው ዓመታት፣ በአንዳንድ መጽሔቶች ካስነበባቸውና፣ "Voices from the past" በሚል ርዕስ፣ መመረቂያ መጽሔታችን ላይ ከሠፈሩት

ግጥሞች ውስጥ:- 'That's how we move away', 'Darkness', 'Poem', 'Memory' እና 'Dilemma' የተሰኙትን በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል:: 'ጩኸት' ለተባለው የዶክተር ፈቃደ አዘዘ የግጥም መድበል ለመጽሀፉ መግቢያነት ያሰፈራቸው ሀረጎችም እሸቱ ለሥነ ጽሁፍ ጭምር የተቀባ ለመሆኑ ጥሩ አማኞች ይመስሉኛል::

እንደ አንዳንድ ሰዎች ጋሼ እሸቱ ማቴሪያሊስት የመሆን አዝማሚያ ጨርሶ አይታይበትም ነበር:: ሙያውን ለንግድ ብቻ ከመጠቀም የተቆጠበ፣ እንደ አንዳንዶቻችን "እንዳች የግል ጥቅም ካላስገኘ ንክች አላደርግም" የሚል አቋም ያልነበረው፣ ባጭሩ የአዳም ስሚዝን የገበያ ህግ (maximizing self-interest) በቀጥታ ወስዶ ለማኅበራዊ ኑሮውም ዋነኛ መመሪያ ያላደረገ፣ መልካም ሰብአዊ ገጽታዎችንም በእጅጉ የተላበሰ እንደነበር በዚህ አጋጣሚ ማንሳት እወዳለሁ:: የበሳልነቱና አርቆ አስተዋይነቱ ልዩ መግለጫ ከሆኑት ሰብአዊ ፀጋዎቹ፣ በጎ አሳቢነቱና ቅን አመለካከቱ፣ ግልጽ፣ ቀጥተኛና ሚዛናዊ አቀራረቡ፣ ትሁት መካሪነቱ፣ ተግባቢ፣ ተጫዋችና ቀልድ አዋቂነቱ፣ ከሌሎች ጋር የመሥራትና የማስተባበር ብቃቱ፣ ለቤተሰቡ፣ ለጓደኞቹና ከሁሉም በላይ ግን ለሀገሩና ለህዝቡ ያሳየው የነበረው ርህራኄና ፍቅር በተለይ ሊወሱለት የሚገባ ይመስለኛል::

በይሉኝታ ቢስነት ሀብት ለማግበስበስ፣ በዚህም ኑሮውን ለማደለብ አልነበረም ጋሼ እሸቱ ደፋ ቀና ይል የነበረው:: በኔ እምነት፣ ጋሼ እሸቱ ያልነበረው አንድ ነገር ካለ ይህ ብቻ ነው:: ለገንዘብና ለጊዜያዊ ጥቅም ያረበደ ሰብእና ስላልነበረው፣ ፍላጎቱና እድራጎቱ ሁሉ፣ በብልጣብልጥነት ለመጠቀም ሳይሆን፣ በመተሳሰብ ለመጠቃቀም በመሆኑ፣ ሀብት ለማካበት ብቻ ለምንሩዋሩዋጥ ኅሊናችንን ሳንዳፍታ እንድንመረምር በጋሼ እሸቱ ሞት እንገደዳለን:: ፍላጎቱንና ድርጊቱንም ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ማግኘት የሚገባውንና የሚችለውን ብቻ ግልጽና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ለማግኘት የሚሻ ሰው ነበር:: በመሆኑም፣ እኔ እስከማውቀው፣ በተሠማራበት የሥራ መስክም ሆነ በሌላ ህይወቱ፣ በዙሪያው ካሉ ሌሎች ሰዎች ጋር፣ ሆን ብሎ የማያስፈልግ ግጭት የመፍጠርና የመነቋቆር አዝማሚያ አይታይበትም ነበር:: ይልቁንም፣ የዋህነቱ፣ መልካም ምኞቱና ሰናይ ምግባሩ ይህን ለመሳሰለው ትብታብ አሳልፎ ይሰጠው እንደነበርና በዚህም ያዝን እንደነበር መመስከር እችላለሁ::

በሌላም በኩል፣ ጋሼ እሸቱ በእውቀትና በልምድ እጅግ የበለጸገ ቢሆንም፣ የግብዝነትና ሌሎችን (በተለይም የበታቾቹን) የመናቅ ባህርይ አይታይበትም ነበር:: በማን አህሎኝነት ልቡ ያላበጠ፣ ደጅ በማስጠናት የማያምን፣ እንደዚሁም ቀድሞ በመወለዱ ብቻ ታሪክ የሠራ የሚመስለው ዓይነትም አልነበረም:: ደረቱን ነፍቶ፣ እየተመፃደቀ በፌዝ፣ 'ድሮ በኛ ጊዜ ቀረ' በሚለው የባዶ ቀፎዎች ከንቱ ሙሾ እራሱን የማይደልል፣ 'በእኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል' መሰሉ የተንኮል ደባ የማይታማ፣ እውቀቱንና ልምዱን በቅንነትና በጥሩ አባታዊ ትህትና ለጀማሪዎችና ለወጣት ምሁራን የማካፈል ከፍተኛ ፍላጎት የነበረው ቀናኢ ምሁር ነበር:: የለውጥ ፍላጎትና ጉጉት ሁሌም አብረውት በመኖራቸው፣ የወጣት ምሁራንን አዳዲስና ገንቢ ሀሳቦች (የአናናር ዘዬዎችም ሳይቀሩ) ከመናቅና ከማንቋሸሽ ብሎም በግትር አዛውንቶች ዓይን (conservative lens) የጎሪጥ ከመመልከት ይልቅ፣ በተቻለው መጠን ድሮን ከዛሬ አጣጥሞ ለመጋዝ ይሞክር ነበር:: የአዳዲስ ግኝቶችና ክስተቶች ባይተዋር በመሆን ፈንታ፣ በተቃራኒው አስፈላጊና ጠቃሚ ሆኖ ካገኘው ከጊዜው ጋር ለመኼድ እልህ ውስጥ ሲገባ ነበር የሚታየው:: ወደ ነፈሰበት የመንፈስ፣ የወላዋይና አድር ባይ ባህርይ ነበረው ማለቴ እንዳልሆነ ግን ይታወቅልኝ:: ፈፅሞ! አጉል ግትር ወይም conservative እንዳልነበረ ለመግለጽ ያህል ነው::

ጋሼ እሸቱ ጥሩ የአንድነት ተምሣሌትም ነበር ማለት እችላለሁ:: ከጠባብ ብኄረተኝነት የፀዳ፣ ዙሪያውን በማጠር የማያምን፣ በሩ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ወይም ፆታ ሳይለይ ለሁሉም ክፍት ነበር:: "እንድ ሰው ብዙ እያነበበና ዓለምን ይበልጥ እያወቃት በኼደ ቁጥር የየትኛው አካባቢ ወግና ልማድ ተገዥ መሆኑን እንኳን ይሰታል" የተባለውን እውነታ በተግባር ካረጋገጡልኝ ሰዎች አንዱ ጋሼ እሸቱ ነው:: በተለይ ጠባብ ጠበብነት እያየለ፣ እንደተላላፊ በሽታ እየተስፋፋ፣ ቀንደኛ የሀገር ዕድገት ሳንክ እየሆነ መምጣቱ ባሳሰበኝና ባሳዘነኝ ጊዜ ጋሼ እሸቱን በመሰሉ ምሁራን ነበር የምጽናናውና ተስፋ የማደርገው::

ጋሼ እሸቱ ለሁሉም ነገር ጊዜ ነበረው:: ሁሉንም ነገር አቀናጅቶ የመሥራት ችሎታው የላቀ ነበር:: የጊዜ ስሌዳው በሥራ መጨናነቁ ከቤተሰቡ ጋር የሚያጠፋው ጊዜ ፈፅሞ አላሳጣውም:: በተጨማሪ፣ ጊዜውን ለዚህ ተግባር በምን መልኩ መጠቀም እንዳለበት አሳምሮ ያውቅበት እንደነበር፣ ለቤተሰቡ በተለይም ለልጆቹ ያሳይ ከነበረው የሚያስደንቅ ፍቅር መረዳት የሚቻል ይመስለኛል:: ለምሳሌ ተማሪው በነበርኩበት ዓመት፣ በሱ ስለተሰጠን አጭር ጥናት (term paper) ምክር ልንጠይቀው ከጓደኞቼ ጋር ቢሮው ዘው ስንል (ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ ነው)፣ ከጠረጴዛው በስተግራ ከተቀመጠ አንድ ቆንጆ ባለቀለም ፎቶ ላይ ነበር ዓይኖቹ ያማተሩት:: በዚያን ቀን፣ ፎቶው የማን እንደሆነ ባለማወቄ ከቁብ አልቆጠርኩትም ነበር (በኋላ ግን የመጀመሪያ ልጁ የህሊና ምስል እንደነበር ነው የተረዳሁት):: በሌላ ቀን፣ በተመሣሣይ ሁኔታ፣ ከቢሮው ኮሪደር ደጃፍ ተኮልኩለን መምጣቱን እየተጠባበቅን ሳለን፣ ፎቶ ላይ ካየናት ትንሽ ልጅ ጋር እየተሩዋሩዋጠ ብቅ ሲል ባስተዋልን ጊዜ (እሱም ልክ እንደ ትንሽ ልጅ) ገርሞን ማንሾካሾካችን ትዝ ይለኛል:: "አቤት! ሲያስቀኑ!" እየተባባልን፣ ባየነው ልብ የሚነካ ያባትና ልጅ የፍቅር ትርኢት:: ሌላ ምሳሌ ለማከል ያህል፣ የዛሬ ስድስት ዓመት ገደማ፣ አንድ ኮንፈረንስ ላይ ለሶስት ተከታታይ ቀናት

ባደርንበት አጋጣሚም፣ የልጆቹ ነገር እንደማያስችለው ተገንዝቦ ነበር። ከሦስቱ ቀናት ሁለቱን፣ አዲስ አበባ እያደረ ንጋት ላይ ለስብሰባው ይመለስ ነበር። እኔ ነገሩ ቢገባኝም፣ እሱ ግን ለማንም ሳይናገር ሹልክ ብሎ ነበር የሚኼደው።

(.... ይቀጥላል)

"ይህች ማስታወሻ በዚህ መልክ ከመቅረቧ በፊት፣ ከውድ ጊዜያቸው ሽርፈው፣ ረቂቁን በማንበብ፣ ጠቃሚ ሀሳቦችንመስጠት ለተባበሩኝ ለዶ/ር ዓለማየሁ ሥዩም፣ ለአቶ ሳሙኤል አስናቀ፣ በተለይ ደግሞ ለጋሼ ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር) ምስጋናዬ የላቀነው። ለማንኛውም ዓይነት ግድፈት ተጠያቂው እኔ ነኝ።

# Food Security & Rural Land Policy : A Discussion

## Food Self-Sufficiency & Food Security: A Brief Comment.

Ato Getachew Yoseph
Department of Economics, Addis Ababa University

The issue cited above presents, among other things, articles and commentaries/queries on the subject by researchers, officials of policy-making government institutions and several participants. I congratulate the panellists and all the others for sharing their views with a wider public and the organisers too for initiating a tradition of constructive policy dialogue.

Understandably, the papers are very brief and as a result one cannot squeeze out satisfactory answers to questions that may cross his/her mind in the process of reading the pieces.

I will therefore start off my queries with very broad definitions of the notions of food self-sufficiency, food security and structural food deficiency in order to place the problematics in the proper context.

Food self-sufficiency refers to the capacity of a country to produce enough or more to meet the food requirements of its population in a normal year at the aggregate level. Here distribution or food entitlement is not a central issue. In other words, food self-sufficiency does not necessarily mean that each member of society or household has access to food. It is possible for a food self-sufficient or even food-surplus country to have several million people who either produce far below the minimum requirements of the household and/or lack the purchasing power to meet their requirements. This category of people are said to be food insecure.

On the other hand, the concept of food security implies a situation where every household is able to feed itself either through purchase from domestic or external supply and/or self-production. Food security is, therefore, an overall development issue while food self-sufficiency is sector-specific -- specific to agriculture.

Some writers also make reference to the concept of structural food deficiency, which underlies the failure of a country to meet the food requirements of its population either through domestic production and/or commercial imports on a regular basis.

In light of this contextual background, the whole thrust of the round-table discussion appears to revolve around the food self-sufficiency side of the problem. I contend this view for two reasons. The very topic of discussion, namely food security and rural land policy, has implicitly narrowed down the problematics of food security to that of increasing agricultural output which may arise as a result of privatisation of rural land. The other reinforcing factor is that the various recommendations advanced by the panellists, viz. change in the rural land tenure system and the envisaged government strategies of extension services may be favourable for expanded food production albeit the fact that the relationship between privatisation of land and the promotion of food security (as defined above) is not clearly articulated. On the other hand, the shift from the traditional approach of extension services, which targeted mainly the surplus-producing areas, to also reach the drought-prone, semi-arid zones and other vulnerable areas can greatly assist in promoting food security.

The point I am trying to make is this. As in the topic itself, all strategies that were mapped out by the panellists are agriculture-sector-targeted. But the issue of food security in the Ethiopian context appears to be one of an overall economic development agenda. Had the theme of discussion not been trimmed to 'food security and the land question', a more instructive exchange of views could have emerged. But admittedly, Dessalegn has lightly touched upon the broader issues in his closing statement. I, therefore, suggest that the EEA revisit and follow up the issue of food security within a broader framework.

## Food Security Constraints in Ethiopia: Some Results from Sample Survey of Three Woredas

Dr. Wolday Amha

This comment has been prepared following the round-table discussion on "food security and rural land policy in Ethiopia". An attempt is made here to provide facts and figures from sample survey results of three woredas in Northern Ethiopia, namely, Habru and Gonder Zuria Woredas in Amhara region and Ofla Woreda in Tigray region. A sample of 288 households were interviewed in 1997 to identify and rank major constraints to food security at household and village levels.

The sample survey results indicate that land holding size is the main constraint (84%) for achieving food security. There are also other important constraints such as high prices of inputs (67.4%), insufficient rainfall (64.2%), high population growth (62.8%), pest and disease (35.8%), land degradation (35.4%), malaria (33.3%), limited access to credit (28.8%), etc. which affect the level of food security. Although the major problems of food security are essentially the same in the three sample Woredas, there are some variations among Woredas in the ranking of food security constraints. For example, the major constraints to food security in Habru Woreda are insufficient rainfall followed by land shortage, high population growth, land degradation and deforestation, pest and diseases, high inputs prices, abnormal weed, access to credit, etc. For Ofla Woreda the major constraints are high price of

inputs, followed by land shortage, insufficient rainfall, high population growth rate and instability in output prices. In Gonder Zuria Woreda the major constraints are land shortage, followed by high price of inputs, malaria, high population growth rate, insufficient rainfall, pests and diseases, abnormal weed, etc. The major causes of food insecurity in rural Ethiopia are summarised in Figure 1. However, the causes of food insecurity varied from time to time and from region to region (the spatial and time dimension of food insecurity).

*Figure 1: Causesof Food Insecurity In Rural Ethiopia*




The main constraints to crop production are high prices of input (73%) followed by insufficient rainfall (62.5%), pests and diseases (37%), limited access to credit (32.6%), and low output prices (17.9). Farmers do not consider the unavailability of input (fertiliser and improved seed) and labour as major constraints. There are differences between Woredas in ranking the crop production constraints. For example, in Gonder Zuria Woreda, the main constraints are high prices of input followed by limited access to credit and insufficient rainfall. In Habru Woreda, the main problems are inadequate rainfall followed by pests and disease, high input prices and limited access to credit. The Woreda level household constraint analysis will guide policy makers

to emphasise on micro level interventions.

The major constraints to livestock production in the sample Woredas are feed shortage (60.4%) followed by overgrazing (53.5%) and disease (16.7%). The problem of low productivity of the indegenous breeds is not felt as a serious problem by the sample farmers. It is clear that farmers can not identify such type of problems because they don't have any other reference with which to compare the productivity of their livestock. The ranking of the livestock constraints are found to be the same in all the three Woredas.

In comparison with the expansion of irrigation, breeding higher yielding varieties and protecting crops and livestock against diseases, the awareness of policy makers on what constitutes an improvement in marketing and infrastructure in order to achieve food security is not given proper attention. There has been very limited effort by the development agents, agricultural experts and policy makers at woreda, zone, and killel levels in using market development as vital element in the development process as well as in the whole exercise of achieving food security. This has been reflected in the draft food security strategies of Tigray and Amhara regional governments drafted in 1997. These regional food security strategies have not given due attention to the development of regional and inter-regional trade and market integration as a tool for achieving food security. The entire emphasis of the food security strategies is on improving the production technology of the drought-affected regions and increase agricultural production or availability within the woredas.

The strategies of achieving food security should include intensifying the use of the relatively abundant resources, particularly land and labour, through the use of modern input in the package program (this would include packages of crop production, livestock, and post-harvest technology); promote and expand marketing and market-oriented production; provide credit to producers wishing to buy inputs; maintaining sound macro-economic and population policies; hold or lower food prices through increased production and reduced cost of marketing; encourage rapid growth of small business enterprises that create jobs; promote agricultural export; develop supplementary employment/income schemes; expansion of targeted programs (for very poor and vulnerable groups); national health and education interventions, and developing emergency capabilities.

## ስለ ምግብ ዋስትናና የመሬት ይዞታ ሁኔታ ለተደረገው ውይይት የቀረበ ማስታወሻ

ዶ/ር ጠንክር ቦንገር
የኢኮኖሚ ፖሊሲ ጥናት ማዕከል፣ ኡጋንዳ፣ ካምፓላ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማኅበር መሠረታዊ በሆኑ የሀገሪቱ፡ የልማት ችግሮች ላይ ባለሙያዎችን በማወያየት ለጀመረው ተግባር ምስጋናዬን አቀርባለሁ:: በተለይ በቅርቡ "የምግብ ዋስትናና የመሬት ይዞታ ሁኔታ" በሚል ርእስ የተካሄደው ውይይት የተለያዩ ባለሙያዎችን በማሳተፍና በአማርኛ ቋንቋ ጭምር መቅረቡ ለሌሎችም ምሁራን ተሳትፎ ፈር ቀዳጅ ነው ማለት ይቻላል:: ይህ አጭር ማስታወሻ የቀረበው ከአስተያየት ሰጪዎች እንደተጠቀሰው የትኩረት አቅጣጫ ለማመልከትና የመሬት ይዞታን በሚመለከት ደግሞ ሌላ አማራጭ እንዳለም ለመጠቆም ነው::

የምግብ ዋስትና ምንጮች ማምረት፣ መግዛት፣ የማኅበራዊ ዋስትና/ድጎማ፣ እርዳታ/ምፅዋትና የነዚህ ቅንጅት ናቸው:: አብዛኛው ለረሀብ የሚጋለጠው የኢትዮጵያ ገጠሬ ከራሱ ምርት

ቤተሰቡን የሚመግብ ነው:: ከነዚህ ውስጥ ጥቂት ባለተረፈ ምርት ሲሆኑ፡ በጣም ብዙ ደግሞ መጠነኛ ሻጭና ገዥ መሀከለኛ አርሶ አደሮች ናቸው:: በሌላ በኩል ቁጥራቸው ከከተማ የእህል ሸማቾች የሚበልጥ ድሀ አርሶ አደሮችና ገና የመሬት ይዞታ ያላገኙ ወጣት ቤተሰቦች ይገኙባቸዋል:: በመጨረሻ የተጠቀሱት በማምረትም ሆነ በመግዛት ሊያገኙ የሚችሉት የምግብ መጠን ከዝቅተኛ አስፈላጊ ፍጆታቸው ያነሰ በመሆኑ በአማካይ ጊዜ እንኳ ረሀብተኛ ናቸው:: ምርት ሲያንስ፡ የእህል ዋጋ ሲንር፡ የጉልበት ቅጥርና ሌሎች የገቢ ምንጮች ሲደርቁ፡ ከረሀብተኛነት ለሞት ይጋለጣሉ:: ሀገራዊ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የበለጠ የፖሊሲ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው እነዚህ ድሀ አርሶ አደሮች ናቸው:: ሌሎች ከምርታማነት ማዘቅዘቅ ጋር በህዝብ ብዛት የተጨናነቁ፡ የመገናኛ አገልግሎት ያላገኙ፡ እንስተኛና በየጊዜው የዝናብ እጥረት የሚታይባቸው የከብት አርቢዎችና የጠረፍ ስለባ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኙ ህዘቦች ናቸው:: በሌላ አንጻር በሀገር አቀፍ ደረጃ በማምረት፡ በመግዛትም ሆነ በሌላ መንገድ የምግብ ብቃት ቢረጋገጥም፡ በቂሚ ደረጃ የምግብ እጥረት የሚያጋጥማቸው አካባቢዎችና ቤተሰቦች ይኖራሉ:: ከነዚህ ውስጥ በእውኑ ባህላችንና የቴክኖሎጂ እቂም አራሽ ወንድ የሌላቸው፡ በሴቶች የሚመሩ ቤተሰቦችና አረጋዊያን ሊጠቀሱ ይችላሉ::

ቂሚ የምግብ ዋስትና በሌላቸው ወገኖች ዘንድ ለፍላጎት ማሟያ የሚያስፈልገው የምግብ መጠን ከዓመት ዓመት ይለያያል:: ስለሆነም፡ በአጭር ጊዜ ለችግሩ መፍትኄ ሊሆን የሚችለው የእህል ባንክ (እንደ ደም ባንክ) ሊሆን ይችላል:: ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ በጎ አድራጊዎች፡ መንግሥታዊ በጀት፡ የአካባቢው ህዘቦችና ሌሎችም አርሶ አደሮች ቂሚ የእደራ ገንዘብ (Trust Fund) አቂቁመው የነፍስ አድን፡ የመቂቂሚያና የልማት ዘርፍ ከትርፉ ማካኼድ ይችላሉ:: ከፍተኛ ጉድለት ሲያጋጥም ኢክፒታሉ በከፊል ለዚሁ ሊውል ይችላል:: ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ የእርሻ ምርት አንፃር በመሀከለኛና በረጅም ጊዜ የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ መሠረቶች በእርሻ ቴክኖሎጂ አጋዥነት የመሬትና የጉልበት ምርታማነትን መጨመር፡ ሰላምና፡ በፖለቲካ ድርጅቶች መሀከል የመደማመጥ ዲሞክራሲያዊ ባህል መስፈን ናቸው:: ለቴክኖሎጂ ዕድገት ደግሞ የገጠር መንገዶች፡ የማባተ ምርት ስርጭትና በገበያ ኃይል መሠረት የሚራመድ የዋጋ ሂደት ወሳኝ ደጋፊ እርምጃዎች ናቸው:: የምግብ እህሎች ዋጋ በአንድ በኩል የተረፈ ምርት አምራቾችን ቅስም እንዳይሰብር፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከሸማቾች አቅም በላይ እንዳይሆን፡ የገበያ ሂደት ከፖሊሲ ጋር የሚጣጣምበት የማስፈጸሚያ መሣሪያ (Policy Instrument) ያስፈልገዋል::

**እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን፡ ከሀገሪቱ ሌሎች የፖሊሲ ግቦች፡ ማለትም፡ እድገት፡ እኩልነት፡ የአካባቢ ጥበቃ፡ የሴቶች መብት፡ ብኄራዊ የክምችት መዳበር ጋር በየፈርጁ ማጣጣምና** ማገናዘብ ያስፈልጋል:: የመንግሥትና የገበያ ሚና ሚዛን፡ ከመሬት ይዞታ ጥያቄ፡ ከሥነ ህዝብ ፖሊሲ፡ ከቴክኖሎጂ፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከኢንዱስትሪ ዕድገትና ልማት ጋር ያለው እስትራቴጂያዊ መስተጋብራዊነትና ማስላት ይጠይቃል:: ሰፋ ባለ መልክ ደግሞ የሌላውን ዓለም ልምድ ከሀገሪቱ አጠቃላይ የልማት ግቦች ጋር ለማገናዘብ ቢቻል፡ ተግባራዊ በሆነ መልክ ከስህተት ለመማርና አመርቂ ውጤቶችን በሥራ ላይ ለማዋል ያግዛል:: የምግብ ዋስትና ፖሊሲ እንደኩሬ ውኃ በአንድ ቦታ የረጋ ሳይሆን ከኢኮኖሚ፡ ከማኅበራዊና የቴክኖሎጂ ዕድገት ሂደት ጋር በየጊዜው እየተገመገመ ማሻሻያና ክለሳ ሊደረግለት የሚገባ ጉዳይ ነው::

ውይይቱ ይበልጥ ያተኮረው የዘመናችንን ሶስት መንግሥታት የመሬት ፖሊሲ በማነፃፀር ለገጠር የምግብ ዋስትና ይበልጥ አመቺው መሬት በግል ወይስ በመንግሥት ቁጥጥር ቢሆን ነው የሚል ይመስላል:: የመሬት ይዞታ ሁኔታ የርእሱ ግማሽ ክፍልና መሠረታዊ ቢሆንም፡ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው መጀመሪያ የምግብ ዋስትና ፖሊሲ የሚቀረጽባቸው መንደርደሪያዎችን መተንተኑ ለውይይቱ የበለጠ የማነጣጠሪያ ዒላማ በሰጠው ነበር:: የሁለቱም ፋይዳ ሊለካ የሚችለው ወደ ተተለመው ግብ ለማድረስ በሚኖራቸው ጥቅምና ጉዳት አንፃር ነው:: በውይይቱ የተሰነዘሩት ሀሳቦች በ1966 ዓ. ም. አብዮት ዋዜማ በግልጽና በድብቅ ይካኼዱ የነበሩትን ውይይቶች ያስታውሳሉ:: በቅድመ አብዮት "መሬት ለአራሹ" ለተባለው ታሪካዊ መፈክር በምሥራቃዊያን ርእዮትና ፖለቲካ በመመርኮዝ የተሰጠው መልስ "መሬት በመንግሥት" የሚለው ነበር:: አሁን ደግሞ የዘመኑን ነፋስ በመከተል "መሬት ለገበያ" የተካው ይመስላል::

በ1960ዎች የመጀመሪያ ዘመናት በጭላሉ በግልጽ እንደታየው ከአዲስ ቴክኖሎጂ የተገኘ የእርሻ ልማት ትርፋማነት እየጨመረ በኼደ ቁጥር፡ እንስተኛ አርሶ አደሮች ከሚያርሱት መሬት በገፍ ይነቀሉ እንደነበር ይታወሳል:: ከኢጣልያ ወረራ በፊት እንደነበረው አዲስ መሬት እንዳያቀኑ መሬት አስቀድሞ 'ይያዝ' ነበር:: ዕድለኛ ሆነው ወይም በሌላ ምክንያት ያልተቀነሱት ከምርታቸው ከ30-60% ያላነሰውን ለጉልተኛ፡ ለነፍጠኛና ለዘመናዊ የመሬት ከበርቴዎች ይገብሩ እንደነበር ወጣቱ ትውልድ ሊያውቀው ይገባል:: ያ ሂደት ከፖለቲካዊ፡ ማኅበራዊና ባህላዊ ጭቆናው ጋር ለምግብ ዋስትና መረጋገጥም ከፍተኛ እንቅፋት ነበር:: ከአፄው ዘመን የተገነዘብነው፡ በሌላው ዓለም በተለይም በላቲን አሜሪካና በደቡብ እስያ እንደታየው፡ በሲቪል ኅብረተሰብ ያልተገደበ የፖለቲካ ሥልጣን ከ"ነፃ" የገበያ ኢኮኖሚ ጋር ሲቀናጅ የብዙሀን አርሶ አደሮች መሬት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ፖለቲካና የኢኮኖሚ መደቦች ሊዛወር እንደሚችል ነው:: የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ክፍለ ኢኮኖሚዎች አመርቂ ዕድገት በማያሳዩበት አገር፡ ከላይ የተገለጸው ሁኔታ ለምግብ ዋስትና መቅርቅዝ ዋናው መንገድ ነው::

በደርግ ዘመን የወጣው የመሬት አዋጅ የማረስ መብትን ለሁሉም አርሶ አደር ማከፋፈሉ ከፍተኛ አዎንታዊ ውጤት የታየበት መዋቅራዊ ለውጥ ነበር። ምናልባት ከቻይና ቀጥሎ በዛሬ ሶስተኛ ዓለም ሀገሮች ከሁሉም ይበልጥ የአርሶ አደር የማረስ መብት የተረጋገጠባት አገር ኢትዮጵያ ናት። ይሁን እንጂ የደርግ መንግሥት የወቅቱን ኢትዮጵያዊና አፍሪካዊ ስልተ ምርት ይዞት በቅጡ ባለመረዳት በገንዘብ ቀጥሮ ማሠራትን በማገድ፤ የእርሻና የኢንዱስትሪን የምርት ዋጋ በመወሰን፣ ባልተቀነባበረ ሁኔታ ከገበያ በመግባትና በመውጣት የተጫወተው ሚና በአንድ በኩል የተረፈ ምርት አምራቾችን ምርታማነት ሲያኮላሽ፣ የፈጠረው ከፍተኛ የድብቅ (ህገ ወጥ) ገበያ፤ (parallel market) ሸማች ድሀ አርሶ አደሮችን ጨምሮ በበላተኛ ዘንድ ከፍተኛ አሉታዊ ውጤቶችን አስከትሎ ነበር። በየትኛውም ሥርዓተ መንግሥት ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ሁኔታ ዋናው የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ መሣሪያ የመሬት ዋስትናና የማያቋርጥ የእርሻ ቴክኖሎጂ ግስጋሴ ናቸው። ደርግ መሬትን የመንግሥት በማድረግ በአርሶ አደሩ ዘንድ የባለቤትነትን ሚና በማኮሰስ የመሬት ባዕድነትን (land alienation) ከማራመዱም በላይ የእርሻ መሣሪያ፤ የምርትና የጉልበት ዋጋና ስርጭት ፖሊሲው የሀገሪቱን የእርሻ ምርታማነት ዕድገት እስር ቤት አስገብቶት ነበር ማለት ይቻላል።

የአሁኑ መንግሥት በእርሻ ምርት መሣሪያዎች አቅርቦት፣ በምርት ዋጋ አኪያኼድ፣ በገንዘብ ቀጥሮ የማሠራት ሁኔታ፣ በብድር ፖሊሲ፣ ወዘተ ... የወሰዳቸው እርምጃዎች በደርግ ዘመን የተፈጠሩትን ማነቆዎች በመፍታታቸው የእርሻ ልማት የተሻለ እንቅስቃሴን አሳይቷል። በቅርቡ በተለይ በበቆሎ ምርት የታየው ሁኔታ የሚያሳየው፣ ከሌላ ደጋፊ እርምጃዎች ጋር፣ የገበያ ኃይሎች የእርሻ ምርትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ሚና ሊኖራቸው እንደሚችል ነው። ነገር ግን አሁንም የመሬትን ይዞታ በመንግሥት ሥር ማቆየቱ ለእርሻ ልማት በዚያም በኩል ለእህል ዋስትና ፈጣንና ዘላቂ ድርጅታዊ ሁኔታ መሆኑ አጠራጣሪ ነው። የየጊዜው ድልድል በባህላዊ የህዝብ ድርጅቶች ፋንታ በመንግሥት ቢሮክራቶች ስለሚሆን፣ ይህ ሂደት የመሬትን የባለቤትነት አለኝታንና ባህላዊ ሚናውን ስለሚሸረሽር ለመሬት የሚደረግለት እንክብካቤ ያንሳል። በደርግ ዘመን የተጀመረው የመሬት ባዕድነት ሁኔታ ይቀጥላል። በተለይ በኢትዮጵያ ሥልጣናዊ የፖለቲካ ባህል ሂደት ውስጥ የአርሶ አደሩ የመሬት ባለቤትነት አጠራጣሪ ስለሚሆን በመሬት ላይ የረጅም ጊዜ መዋዕለ ንዋይ የማፍሰስ ዕድገትን ሊገታ ይችላል። የገጠርና የከተማ የሰው ኃይል ስርጭት ለጠቅላላ ኢኮኖሚ ልማት በሚያግዝ መንገድ እንዳይሸጋሸግ ያግዳል። ለእርሻ ልማት ብድር ዋስትናነቱ አስተማማኝ አይሆንም። ከመንግሥት ባለቤትነት ወደ ህዝባዊነት የሚወስደው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ድልድይ ብዙ የተወሳሰበና እርግጠኝነቱ በውል ሊታወቅ የማይችል ነው።

ስለሆነም የመሬት ይዞታና አጠቃቀም ድልድል ውይይትን በመንግሥትና በገበያ መሀከል ከመከለል ፋንታ የአካባቢን ዋስትና የሚያለብሱትን ባህላዊ ድርጅቶችን ቢጨምር የተሻለ ነው። ከቦታ ቦታ መጠነኛ ልዩነት ቢኖርም፣ በመላ ኢትዮጵያ የገጠር አካባቢዎች፣ ከኢኮኖሚና ፖለቲካ ሚናው ባሻገር መሬት የአለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን ትውልድ የሚያገናኝ ዘላለማዊ ሰንሰለት ነው። እያንዳንዱ አካባቢ መሬትን፣ የሰው ጉልበትንና፣ ተሸራራፊና የማይሸራረፍ ካፒታልን (ለምሳሌ በሬ) በአጭርና በመሀከለኛ ጊዜ የሚያደላድል ሥርዓት አለው። የባህላዊ ድርጅቶች ብቃት ከላይ ለተጠቀሱት ግቦች በቂ በማይሆኑበት ጊዜና ቦታ መንግሥታዊ ማሻሻያና መመሪያ ሊደረግላቸው ይገባል። በዚህም መሠረት በገበያ ዋጋ አማካይነት የመሬት ጥቅም (use value) ማረስ ወደሚፈልጉና ወደሚችሉ አምራቾች ይሸጋሸጋል። የመንግሥት ግትርና ፍጹማዊ ሥልጣን በባህላዊ ድርጅቶች ይገራል። በአነስተኛ አርሶ አደሮች መሬትን መሸጥና መለወጥ ሊያመጣ የሚችለውን ሰፊ የተበላላጭነትና የምግብ ዋስትና መሸርሸርን ለመግታት ግብይቱን በመሬቱ ጥቅም ብቻ በመገደብ የእርሻ ዕድገትንና በዚያም በኩል የምግብ ዋስትናን የሚያረጋግጥ የልማት ሥርዓታዊ ደምብ (institutional framework) መዘርጋት ይቻላል። ስለዚህ ገበያንና መንግሥትን እንደተፃራሪ አማራጭ ከማቅረብ ፋንታ፣ የገበያ ኃይሎችን ምርታማነት አራማጅነትንና የምርት ኃይሎችን በበለጠ ፍሬያማነት የማደላደልን ሚና (allocative efficiency) ከባህላዊ ድርጅቶች አለኝታነትና ተጨባጭ የመሬት ዋስትና አስጠባቂነት ጋር በማገናዘብ የመንግሥትን አቀነባባሪነት ሚና መቅረጽ ይቻላል።

ይህን ማለት ግን የምግብ ዋስትና የሚያስገኝ እስትራቴጂ በአርሶ አደሮች አመራረት ስልት ብቻ ይወሰን ማለት አይደለም። መሬት በገፍ በሚገኝባቸው ቀበሌዎች የአካባቢው ህዝብ መብት በህግ የተጠበቀ ሆኖ ሰፋፊ እርሻዎችን ማስፋፋት ይቻላል። በዚህም አማካይነት የሥራ ዕድል ከመጨመር፣ ከዋጋ መስተካከል፤ የውጭ ንግድን ከማሳደግ ተግባሮች ጋር የምግብ ዋስትና መሠረቶች አድማስ ይሰፋል።

